# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 105 ግንቦት 12 ቀን 2002 ዓ.ም

አንብበው
ያስነብቡ!
አባዝተው
ያሰራጩ!

ምርጫን እንደመሰለያ መሳሪያ የሚጠቀመው ወያኔ በድህረ ምርጫ 97 በህዝባችን ላይ የፈጸመው አይነት ፋሽስታዊ ጭፍጨፋ እንዳይደገም ከተፈለገ ነጻ እና ገለልተኛ የሆነ የምርጫ አስፈጻሚ አካላት፤ ለሁሉም እኩል የሚያገለግል የሚዲያ አገልግሎት፤ ታማኝነታቸው ለህገመንግሥቱ ብቻ የሆነና ከፖለቲካ ወገናዊነት የጸዱ የፖሊስ፤ የመከላኪያና የደህንነት ተቋማት መመስረት ይኖርበታል።

ለወያኔ እድሜ መራዘሚያ ህጋዊና ሞራላዊ መሰረት እንዲያስገኝ ታስቦ በሚካሄድ ምርጫ መሳተፍ ለህዝባችን የሚያስገኘው ፋይዳ አይኖርም!!!

## ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ ለፖለቲካ ፍጆታ ሲል ሰዎችን እንደሚያስገድል መረጃ እንዳለ ተገለጸ

ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ ለፖለቲካ ፍጆታ ሲል ሰዎችን እንደሚያስገድል መረጃ አለ ሲሉ ከምርጫ 97 በኋላ የተመሰረተው አጣሪ ኮሚሽን ሰብሳቢ ዳኛ ፍሬህይወት ሳሙኤል ገለጹ።

ባለፈው ሳምንት ለዜና ድረ-ገጾች በላኩት ጽሁፍ፣ ወያኔ ለፖለቲካ ፍጆታ ሲል በድህረ-ምርጫ 97 ፖሊሶችን ስለማስገደሉ እና በብሔረሰቦች መካከል ግጭቶችን ስለመጫሩ መረጃ እንዳለ ገልጸዋል። ዳኛ ፍሬህይወት ከምርጫ 97 በኋላ በንጹሃን ዜጎች ላይ የተደረገውን ግድያ ለማጣራት የተመሰረተው ኮሚሽን ሰብሳቢ ነበሩ።

በወቅቱ፥ ኮሚሽኑ በድምጽ ብልጫ የወያኔ የደህንነት ሃይሎች ተመጣጣኝ ያልሆነ ሃይል ተጠቅመዋል ብሎ በመወሰኑ ያልተደሰተው ወያኔ፤ ውሳኔው እንዲቀየር በአባላቱ ላይ ካደረሰው ማስፈራሪያ የተነሳ ዳኞች ፍሬህይወት ሳሙኤል እና ወልደሚካኤል መሸሻ በኮሚሽኑ የድምጽ አሰጣጥ ሂደት ወቅት የተቀረጸውን ቪድዮ እና ሌሎች ሰነዶች ይዘው ከአገር መውጣታቸው ይታወሳል። አገዛዙም በነሱ ምትክ የራሱን ሰዎች ተክቶ የሚፈልገው ውሳኔ እንዲተላለፍ ማስደረጉ ይታወቃል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## በመጪው እሁድ በኢትዮጵያ በሚካሄደው የምርጫ ተውኔት ውድድር እንደማይኖር ተገለጸ

በአሜሪካ ያሉ የአፍሪካ ቀንድ ተመራማሪዎች ለአሜሪካ ድምጽ በሰጡት ቃል በመጪው እሁድ የምርጫ ተውኔት ምንም ውድድር ይኖራል ብለው አይጠብቁም።

እነዚህ ተመራማሪዎች፥ ገዢው ፓርቲ ሁሉን ነገር ሙሉ ለሙሉ መቆጣጠሩን እና በ1997 እንዲጋፈጥ የተገደደው አይነት ውድድር እንዳይደገም ማረጋገጡን ገልጸዋል።

ኢ.ቭ ሳንድበርግ የተባሉ ፕሮፌሰር የወያኔ አገዛዝ ሙሉ በሙሉ የሚቆጣጠረውን መገናኛ ብዙሃን በመጠቀም፣ ምን ያህል ከቀድሞው አገዛዝ እንደሚሻል፣ መንገድ መስራቱን፣ አንዳንድ ህንፃዎችን ቀለም መቀባቱን፣ ህዝብ አለመራቡን ያለማቋረጥ ለህዝቡ ይናገራል ብለዋል። በሌላ ጎን ደግሞ ተቃዋሚዎቹ ሙሉ ለሙሉ ሊጠፉ ደርሰዋል የሚሉት እኚህ ፕሮፌሰር፣ መሪዎቻቸው ወይ እስር ቤት፣ ወይ በስደት፤ ወይ ደግሞ እስከ ግድያ፣ እስራትና እንግልት የሚደርሰውን የአገዛዙን ጫና መቋቋም አቅቷቸው ስራቸውን አቁመዋል ብለዋል።

በጉዳዩ ላይ ለአሜሪካ ድምጽ ቃለ መጠይቅ የሰጡት ተመራማሪዎች ሁሉ አገዛዙ ምርጫውን በቀላሉ ያሸንፋል ብለው እንደሚጠብቁ የዜና አውታሩ ገልጿል።

## ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ በመድረክ ፓርቲ ላይ የሚያደርገውን አፈና ቀጥሏል

የምርጫው ተውኔት ሊካሄድ አንድ ሳምንት ሲቀረው፥ ዘረኛው እና አምባገነናዊው አገዛዝ በመድረክ ፓርቲ ላይ የሚያካሄደው አፈና እንደተጠበቀው ቀጥሏል።

ባለፈው ቅዳሜ፣ ግንቦት 7 ቀን፣ ሰላማዊ ሰልፍ ለማካሄድ ፍቃድ የጠየቀው መድረክ፤ በአዲስ አበባ መስተዳደር የወያኔ ሹመኞች "በአደባባይ ስብሰባ ማድረግ አይቻልም" የሚል መልስ እንደተሰጠው ኢትዮጵያ ዛሬ የተባለው የዜና ድረ-ገጽ ዘግቧል። የአሜሪካ ድምጽ ባለፈው አርብ የፓርቲውን አመራር በመጥቀስ እንደዘገበው ደግሞ ፓርቲው በሺዎች በሚቆጠሩ የምርጫ ጣቢያዎች ታዛቢዎችን እንዳያስመዘግብ ተከልክሏል።

የፓርቲው አመራር አባል የሆኑት አቶ ቡልቻ ደመቅሳ ለአሜሪካ ድምጽ እንደተናገሩት፥ መድረክ ታዛቢዎቹን በጊዜው እንዳያስመዘግብ በመከልከሉ፣ በሺዎች በሚቆጠሩ ጣቢያዎች የቆጠራ ሂደት ወቅት (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## በርካታ የቀበሌ ሰራተኞች ስራቸውን እየለቀቁ መሆኑ ታወቀ

በአዲስ አበባ ከተማ በርካታ የቀበሌ ሰራተኞች ወያኔ የምረጡኝ ዘመቻ እንዲያደርጉለት የሚያደርግባቸውን ተጽእኖ በመጥላት ስራቸውን እየለቀቁ መሆናቸውን የአዲስ አበባው ዘጋቢያችን የላከው መረጃ አሳይቷል።

ግለሰቦቹ፥ የአገዛዙ ካድሬዎች ያለማቋረጥ ስብሰባ እየጠሩ ለህዝብ የሚሰጡትን አገልግሎት ትተው በምርጫ ዘመቻ ላይ እንዲያተኩሩ የሚያደርጉባቸው ጫና እንዳደከማቸው ስሞታቸውን አሰምተዋል።

በግዴታ የወያኔ አባላት የሆኑና በምረጡኝ ዘመቻው እንዲሳተፉ የተደረጉ ሰዎች፥ በየሰው ቤት እየዞሩ እንዲያንኳኩ መገደዳቸው በነዋሪዎች አይን ውስጥ እያስገባቸው እና እያሸማቀቃቸው እንደሆነ ስሞታቸውን እንደሚያሰሙ ከአዲስ አበባ ምንጮቻችን የሚደርሱን ተደጋጋሚ መረጃዎች ያሳያሉ።

## የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ድርጅት ስርጭቱን በስኬት መጀመሩ ተዘገበ

በቅርቡ የተመሰረተው የኢትዮጵያ ሳተላይት ተሌቪዥን ድርጅት ወደ ኢትዮጵያና ሌሎች የአለማችን ክፍሎች በአማርኛ ቋንቋ የሚያደርገውን ስርጭት በስኬት መጀመሩ ተዘገበ።

ኢትዮፎረም የተባለው የዜና ድረ-ገጽ ምንጮቹን በመጥቀስ እንደዘገበው፥ የሙከራ ስርጭቱን በሚመለከት በርካታ ምላሾች ከአለም ዙሪያ ለቴሌቪዥን ድርጅቱ የደረሱ ሲሆን፣ ከኢትዮጵያ ክፍላተ አገራት ሳይቀር ብዙ የስልክ መልክቶችን ተቀብሏል።

የቴሌቪዥን ድርጅቱ "ነፃነትን፣ ሚዛናዊነትን እና ተአማኒነትን መመሪያው" ማድረጉን የሚገልጽ ሲሆን፤ ሲመሰረት በተለቀቀው ጋዜጣዊ መግለጫም፣ በተባበሩት መንግስታት የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌ አንቀጽ 19 ላይ የተጠቀሰውን "ሃሳብን በነፃነት የመግለጽ እና መረጃ የማግኘት" መብት ተግባራዊ የማድረግ ግዴታ አለብን ብለው በሚያምኑ ግለሰቦች መቋቋሙ ተገልጿል።

የስርጭቱን ጅማሬ በሚመለከት በተለያዩ መድረኮች ከተሰጡ አስተያየቶች በርካቶቹ፣ አዲሱ የቴሌቪዥን አገልግሎት የወያኔ አገዛዝ በኢትዮጵያ ነፃ መገናኛ ብዙሃን ላይ ከሚያደርገው አፈና የተነሳ የተከፈተውን ክፍተት ይሸፍናል የሚል ተስፋ እንዳላቸው ይገልፃሉ። በኢትዮጵያ በነፃ መገናኛ ብዙሃን ላይ ካለው ከፍተኛ አፈና የተነሳ በርካታ የግል ህትመቶች መዘጋታቸው እና እንደ አሜሪካ ድምጽ ራድዮ ያሉትም መታፈናቸው ይታወቃል። በዚህ ሳምንት አውራምባ ታይምስ የተባለው ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ የሆኑት አቶ ውብሸት ታዬ ከአገዛዙ ባልስልጣናት ከደረሰባቸው ጫና የተነሳ ስራቸውን ለመልቀቅ መገደዳቸውን ለዜና ድረ-ገጾች በላኩት ጽሁፍ አስታውቀዋል።

የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ድርጅት በተለያዩ የአለማችን ከተሞች የድጋፍ ማሰባሰቢያ ዝግጅቶችን ለማካሄድ እንዳቀደና፤ በሎስ አንጀለስ፣ በዋሽንግተን ዲሲ እና በሲያትል ከተሞች፤ እንዲሁም በአሃዮ እና በኮሎራዶ ግዛቶች በመጪው እሁድ ግንቦት 15 ቀን የሚካሄዱ ዝግጅቶች እንዳሉ የድርጅቱ ድረ-ገጽ ላይ የወጣ ማስታወቂያ ያስረዳል።

## በአዲስ አበባ ከተማ ከፍተኛ የወያኔ ጸጥታ ሃይሎች እንቅስቃሴ እንዳለና በከተማዋ አንድ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትም ረብሻ ተነስቶ እንደነበረ ታወቀ

በአዲስ አበባ በኮልፌ ክፍለ ከተማ በሚገኘው ሚሊኒየም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ስድስት ኪሎ ግቢ የተከሰተውን ጸብ ተከትሎ ረብሻ ተነስቶ እንደነበር ታወቀ።

ይህ ዘገባ እስከተጠናከረበት ጊዜ ድረስ በትምህርት ቤቱ የደረሰ ጉዳት ስለመኖሩ ያልታወቀ ሲሆን፤ ረብሻውን ተከትሎ የከተማይቱ መምህራን ተማሪዎች በእረፍት ጊዜያቸው እንኳ የመሰባሰቢያ እድል እንዳይኖራቸው እንዲከለከሉ መታዘዛቸውን የግንቦት 7 ድምጽ ዘጋቢ ከአዲስ አበባ በላከው መረጃ አሳውቋል። በከተማዋ የሚገኙ አንዳንድ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችም በወታደሮች ተከበው መሰንበታቸውን ዘጋቢያችን ጨምሮ ገልጿል።

በተያያዘ ዜናም፥ አድማ በታኝ እና ፌዴራል ፖሊሶች በከተማዋ ውስጥ በብዛት ሲንቀሳቀሱ እንደሚታዩ ታውቋል። በተጨማሪም፥ የግንቦት 7 ድምጽ ምንጮች እንደገለጹት በሺዎች የሚቆጠሩ አዳዲስ የውትድርና ሙያ ስልጠና ምሩቆች በከተማይቱ የተለያዩ ቀጠናዎች በቡድን ተከፋፍለው ሰልፍ ሲያደርጉ ቆይተዋል። በያንዳንዱ ቡድን ውስጥም ከ70 እስከ 100 የሚሆኑ ወታደሮች ተሰልፈው የከተማይቱን ጎዳናዎች ሲያቆራርጡ መሰንበታቸውን እነዚሁ ምንጮች ገልጸዋል።

ዘጋቢያችን ያነጋገራቸው ነዋሪዎች እነዚህን እንቅስቃሴዎች በህዝቡ ላይ እንደሚካሄዱ ማስፈራሪያዎች እንደሚቆጥሩ ገልጸውለታል።

## በ"ምርጫ 2002" ቧልታይ ተውኔት እየተዝናናን ተከትሎት ለሚመጣው መራራ ትግል እንዘጋጅ!!!

"ምርጫ 2002" የተሰኘው ባለሶስት ገቢር ቧልታይ ተውኔት መታየት ቀጥሏል። ከጥቂት ቀናት በኋላ የተውኔቱ ገቢር አንድ ተጠናቆ ተከታዩ - ገቢር ሁለት - ይጀመራል። ገቢር ሁለት ከመጋረጃ በስተጀርባ የሚደረግ ነው፤ ሆኖም ግን እኛ ታዳሚዎቹ ምን እየተደረገ እንደሆነ እናውቃለን - የ546 የፓርላማ ወንበሮች ድልድል። ይህንን ገቢር በጣም አስቂኝ የሚያደርገው ብዙ ፊቶች ባሉት አንድ ተዋናይ ብቻ የሚደረግ መሆኑ ጭምርም ነው።

ተዋናዩ ወያኔ ከ546ቱ የፓርላማ ወንበሮች ውስጥ "ስንት፣ ለእነማን፣ የት ልስጣቸው?" በሚለው ሃሳብ ሲጨነቅ እናያለን። በርካታ በወረቀት የተሞሉ ሣጥኖችን ወደጎን አስቀምጦ ሲያሰላ፣ ሲደምርና ሲቀንስ እናያለን። እኛ ተመልካቶችም በዚህ ቧልት እንስቃለን።

**... ተውኔቱ ቀጥሏል ...**

የወያኔ የወንበር ድልድል ስሌት በሣጥኖቹ ውስጥ ከገባው የመራጭ ድምጽ ቁጥር ጋር ባይመሳሰል ችግር የለውም። እርግጥ ነው ድልድሉ በጣም እንዳያሳጣ በጥንቃቄ መሥራት አለበት። የምርጫ ውጤትን በቶሎ የማሳወቅን አደጋ ወያኔ ከ1997 የአዲስ አበባ ምርጫ ተምሯል። ከያኔው የአዲስ አበባ ስህተቱ በቶሎ ትምህርት ወስዶ የክልሎችን ውጤት በማዘግየት ለራሱ ሰዎች ቁጥር መጨመሪያ ጊዜ አግኝቷል። ያም ሆኖ ግን የ97ቱ የድምፅ ዘረፋ ጥድፊያ የበዛበት ስለነበር በየቦታውም የሚያሳጡ ነገሮች ተከስተዋል። ከዚህም ትምህርት ቀስሞ አሁን ተዝናንቶና ተረጋግቶ ቁጥሮችን ለመሙላት የአንድ ወር ጊዜ ለራሱ ሰጥቷል።

በዚህ አንድ ወር ጊዜ ውስጥ ስለ ምርጫው ውጤት መተንፈስ አይቻልም። ታዛቢዎችም የታዘቡትን መናገር አይችሉም። በዚህ ወቅት ዝም ማለት የሚጠበቅባቸው ተቃዋሚዎች፣ ታዛቢዎችና መራጮች ናቸው። ወያኔ ግን ይህንን ወቅት ለሁሉ-ዓቀፍ ፕሮፖጋንዳ ይጠቀምበታል። እንዲያውም የአገሪቷን ሬድዮ፣ ቴሌቪዥንና ጋዜጦችን በብቸኝነት መያዙ አልበቃ ብሎት ተጨማሪ የፕሮፖጋንዳ መንገዶችን እያፈላለገ ነው።

በ1997 ምርጫ ወቅት ሕዝብ የተጠቀመባቸውን የቅስቀሳ መንገዶች ወያኔ ዘንድሮ ሊሞክራቸው ነው። ከእቅድ ከተያዙት የፕሮፖጋንዳ መሣሪዎች አንዱ በተንቀሳቃሽ ስልኮች የሚተላለፉ አጫጭር መልዕክቶች ናቸው። የምርጫው እለትና በማግሥቱ የሚበተኑ የስልክ መልዕክቶች ተጽፈው ሞባይል ስልክና ካርድ ለተገዛላቸው ምንደኞች ተሰራጭቷል። በድረገፆች የሚሰራጩ ጽሁፎችም ተዘጋጅተዋል። የኢሌክትሮኒክስ ደብዳቤዎችን ለመበተንም በርካታ የኢሜል አድራሻዎች ተዘጋጅተዋል። እንደቢቢሲ ባሉ ድረገፆችም የሚጽፉ ምናባዊ ሰዎች ተዘጋጅተዋል። ተቃዋሚዎች የሚጠቀሙበትን የቅስቀሳ መንገዶች ሁሉ ወያኔ ሊሞክራቸው ቆርጧል።

የዚህ ዘመቻ ዋነኛ ዓላማ የወያኔን የወንበሮች ድልድል የምርጫ ቦርድ ተብየው በመናገሩ በፊት ለእያንዳንዳችን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ እንዲደርሰን ማድረግ ነው። ወሬው ለሁሉም መዳረሱ ሲረጋገጥና ዜናነቱ ጊዜ ሲያልፍበት የምርጫ ቦርድ የተሰጠውን ቁጥር ይፋ ያደርግና ገቢር ሁለት ይጠናቀቃል። ቀድሞ የተሰማ በመሆኑ ቦርዱ የምርጫ ውጤት ነው ብሎ በሚያውጀው ነገር የሚደነግጥ ቀርቶ የሚደነቅም አይኖርም።

ከዚህ በኋላ የድራማው የመጨረሻው ክፍል የሆነው ገቢር ሶስት - ድህረ-ምርጫ - ይጀመራል። ይሄኔ በኢትዮጵያ ዲሞክራሲ ምን ያህል ስር እንደሰደደ አሰልቺ ትንተናዎችን እንጋታለን። ስለ ሕዝብና ወያኔ ፍቅር ብዙ ልብወለድ ታሪኮች እንድንሰማ እንገተጎታለን። በድራማው ክፍል አንድ የተሳተፉ ፓርቲዎች ለአንዳንዶቹ ለተሳትፎ የተሰጣቸውን ጥቂት ወንበሮችን አመስግነው ተቀብለው ፓርላማ ይገባሉ። "በአማራጭ እጦት" መለስ ዜናዊን በጠቅላይ ሚኒስትርነት ይመርጣሉ። ድራማው በወዳጅ አገሮች የደስታ መግለጫዎች ይጠናቀቃል።

ተውኔት የሕይወት ነፀብራቅ ነው። ቧልታይ ተውኔት እንደ መስታወት ግራውን ቀኝ፣ ቀኙን ደግሞ ግራ አስመስሎ በማሳየት ሃቁን ገልብጦ ይሳለቃል። "ምርጫ 2002" ቧልታይ ተውኔት ነው። ታድያ ወያኔ ብቻ አይደለም የቧልታይ ተውኔት ተዋናይ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብም አሳምሮ ይጫወተዋል። ለምሳሌ ሚያዝያ 29 ቀን 1997 ዓም የኢትዮጵያ ሕዝብ ወያኔ ላይ ቧልት ተጫውቷል። ዛሬም እንደያኔው ሁሉ የኢትዮጵያ ሕዝብም የ"ምርጫ 2002" ቧልትን በራሱ መንገድ እየተጫወተው ነው።

ከኢትዮጵያ ሕዝብ አንፃር የምርጫ 2002 ቧልታይ መልዕክት ባጭሩ የሚከተለው ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ የወያኔን ምርጫ ከቁም ነገር አልወሰደውም፤ በተፈጠሩት መድረኮች ግን ምሬቱን ተንፍሶበታል። ወያኔ በፍርሃት እርዶ እንዲቅበጠበጥ አድርጎታል። አንዳንዱ ካርዱን ይወረውርለት ይሆናል፤ ልቡን የሚሰጠው ግን የለም። በአገሪቱ የተሰማሩ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ምርጫ አስፈፃሚዎችና ታዛቢዎች ከወያኔ ውሳኔ ውጭ የሚያደርጉት ነገር እንደሌለ የኢትዮጵያ ሕዝብ ያውቃል። እነዚህ ሰዎች እነማን መሆናቸውና የተመረጡበትም መመዘኛ ይታወቃል። ተቃማሚዎች የምርጫ ታዛቢ እንደሌላቸው ይታወቃል። እናም የሚቆጠር ድምጽ የለምና የልቡን ሳይሆን ለጊዜው የተመቸውን ያደርጋል። ልክ እንደ ሚያዝያ 29 ሕዝብ ወያኔን አሞኝቶ የራሱን ዝግጅት ያጧጡፋል።

የሚያዝያ 29 ቀን 1997 ዓም ቧልትን ተከትሎ የመጣው የሚያዝያ 30 ቀን 1997ቱ ምድር-አንቀጥቅጥ እውነታ ነበር። የምርጫ 2002ን ቧልትንም ተከትሎ የሚመጣው ቁጣ ወያኔን ጠራርጎ እንደሚያስወግድ ጥርጥር የለንም። በወያኔ ቧልታይ ተውኔት እንዝናና፤ ግና ቧልቱን ተከትሎ ለሚመጣው መራራው ትግል ወገባችን እናጥብቅ።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

### ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ዳኛ ፍሬህይወት በዚህ ጽሁፋቸው እንደገለጹት፥ በማጣሪያው ሂደት በአዲስ አበባ በሰላማዊ ሰልፈኞች ተገደሉ ከተባሉት ፖሊሶች ውስጥ የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ በአገዛዙ ሆን ተብሎ እንደተመቱ መረጃ አግኝተዋል። አንድ የፌዴራል ፖሊስ መኮንን ለአጣሪ ኮሚሽኑ በሰጠው መረጃ፥ "መጀመሪያ ላይ ፖሊሶች በሰልፈኞች ላይ ጠንካራ እርምጃ ለመውሰድ ብዙም እንዳልተገፋፉ"፤ በዚህም ምክንያት "እልህ እንዲይዛቸው እና ጨካኝ እርምጃ መውሰድ እንዲችሉ አንድ ሁለታቸው እዚያው ሁከቱ ውስጥ በሌሎቹ ወታደሮች እንዲመቱ" መደረጉን መስክሯል።

በሰልፈኞች ተገደሉ ከተባሉት ዘጠኝ ፖሊሶች ውስጥ አንዱ በሌላ ፖሊስ ባልደረባ ስለመገደሉ ማስረጃ እንዳለ፤ እንዲሁም የተቀሩት ስድስት ፖሊሶች ላይ የተፈጸመው ግድያ ምርመራ ሳይደረግበት፤ አሟሟታቸው "ምንም ፍንጭ እንዳይኖረው፣ አስከሬናቸው ፎቶ ሳይነሳ፣ ሳይመረመር፣ የሰነድ ማስረጃም እንዳይኖር ተደርጎ" መቀበራቸውን የዳኛው ጽሁፍ ያስረዳል።

በተጨማሪም፥ በአዲስ አበባ ከተማ በፈረንሳይ ለጋሲዮን ሰፈር ነዋሪዎች ፖሊስ ላይ ወረወሩት የተባለው ቦምብ፤ በወቅቱ ጥበቃ ይደረግለት ከነበረው እና የትምህርት ሚኒስቴር ከነበረችው ገነት ዘውዴ እናት ግቢ ውስጥ መወርወሩ በምርመራው ሂደት ተረጋግጧል።

ዳኛ ፍሬህይወት፥ ከዚህም ሌላ በወቅቱ ከአዲስ አበባ ውጪ ባደረጓቸው ምርመራዎች የአገዛዙ ካድሬዎች በብሄረሰቦች መካከል ሆን ብለው በጫሩት ግጭት ከፍተኛ ጉዳት ስለመድረሱ መረጃ ማግኘታቸውን ጽፈዋል።

### በአዲስ አበባ ከተማ ከፍተኛ የወያኔ ጸጥታ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

በክፍሉ ውስጥ የሚኖሩት በወያኔ የተመረጡ ሰዎች ብቻ ናቸው። በተያያዘ ዜና፥ ከአውሮፓ ህብረት የተላኩት ጥቂት ታዛቢዎች በአገሪቱ ውስጥ ስለሚያደርጉት ማንኛውም እንቅስቃሴ የወያኔን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ማሳወቅ እንደሚገባቸው በአገዛዙ መታዘዛቸውን ዘጋቢያችን ከአዲስ አበባ በላከው መረጃ አሳውቋል።

በመድረክ ፓርቲ ላይ የሚደረገው ዘርፈ ብዙ ጥቃት ቀጥሎም፥ በአገሪቱ ውስጥ በሚታተሙ በርካታ ጋዜጦች ላይ ፓርቲውን የሚያጠቁ ማስታወቂያዎች በመንግስት መስሪያ ቤቶች ስም እንዲወጡ እየተደረገ መሆኑ ታውቋል። እነዚህ ማስታወቂያዎችም፥ "መድረክ የጀመረውን የአመጽ እንቅስቃሴ የማያቆም ከሆነ የኢትዮጵያ ህዝብ እና መንግስት እርምጃ ይውሰድበት" የሚሉ እንደሆኑ ለማወቅ ተችሏል።

አዲስ አበባ የሚገኘው የግንቦት 7 ድምጽ ዘጋቢ፥ ወያኔ በመድረክ ፓርቲ ላይ እያደረጋቸው ስላሉት ውንጀላዎች ያናገራቸው ግለሰቦች፣ ክሶቹን ካለማመናቸውም ባሻገር ተነሱ ከሚባሉት ጸቦች በስተጀርባ አገዛዙ ብቻ ሊኖር ይችላል ብለው እንደሚያምኑ ገልጸዋል።

በግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ የህዝብ ግንኙነትና ቅስቀሳ ዘርፍ በሳምንት አንዴ የሚዘጋጅ ድርጅታዊ ልሳን

የፖስታሳጥን ቁጥር ፡- POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

ሃይለ ሀሳብ

የግንቦት 7 ድምጽ፣ ቁጥር 105 ግንቦት 12 ቀን 2002 ዓ.ም፤

# ምርጫ ወይስ ጦርነት?

የዘረኛዉና የአምባገነኑ መለስ ዜናዊ ስርአት ኢትዮጵያን ማፍረስና የኢትዮጵያን ህዝብ በዘር መከፋፈል ከጀመረ እነሆ 19 አመታት ተቆጥረዋል። ይህ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት ሰፊ እቅድ ወጥቶለት ደደቢት በረሐ ዉስጥ የዛሬ 36 አመት የተጠነሰሰዉ እኩይ ሤራ በተግባር ተተርጉሞ ዛሬ ኢትዮጵያ ዉስጥ ኢትዮጵያዊነት እየላላ ጎጠኝነት እየጎላ ነዉ።ኢትዮጵያ ዉስጥ በብሔረሰቦች መካከል ያለዉ ዉጥረት ለረጂም ግዜ የዘለቀ ችግር ነዉ ደግሞም በደርግና በኃይለሥላሤ ዘመነ መንግስትም ቢሆን ኢትዮጵያዉያን መብታችንና ነፃነታችን ተከብሮ አያዉቅም፡ ሆኖም በነዚህ ሁለት መንግስታት ዘመን የኢትዮጵያ አንድነትና ኢትዮጵየዊነት አደጋ ላይ ወድቆ አያዉቅም። ዛሬ ወያኔ የሚባል አደጋ አገራችን ላይ ከተፈጠረ በኋላ ግን ኢትዮጵያዉያን በተለይ ወጣቱ ትዉልድ ትኩረት የሚሰጠዉ ለኢትዮጵያዊ ማንነቱ ሳይሆን ለጎሳ ማንነቱ ለአገሩ ለኢትዮጵያ ሳይሆን ለጎጡና ለክልሉ ሆኗል።

ዘረኛዉ መለስ ዜናዊና ጓደኞቹ አዲስ አበባን ከተቆጣጠሩ በኋላ በሙሉ ኃይል ከሰሯቸዉ ስራዎች አንዱና ዋነኛዉ የኢትዮጵያ ህዝብ በተለይ ወጣቱ ትዉልድ ከኢትዮጵያዊት ማንነነቱ  ይልቅ የብሔር ማንነቱ ላይ እንዲያተኩር ማድረግ ነበር። ዛሬ እጅግ ከሚያንገበግቡንና ከሚቆጩን ነገሮች አንዱ የወደፊቷን ኢትዮጵያ የሚረከበዉ ትዉልድ በሚዘጋጅባቸዉ ከፍተኛ ትምህርት ተቋሞች ዉስጥ አንዱ ተማሪ ሌላዉን ተማሪ የሚለየዉ በስሙ፤በእድሜዉ፤በክፍል ደረጃዉ፤ በሚማርበት የትምህርት ዘርፍ ወይም በተመዘገበበት ፋኩልቲ ሳይሆን የ"ኦሮሞ' ተማሪ፤ የ"ትግራይ" ተማሪ የ"አማራ" ተማሪ እያለ ነዉ። በተለይ የኢትዮጵያ ተማሪዎች የመብት፤ የእኩልነትና የነፃነት ጥያቄዎችን በጋራ ባነሱበትና እጅ ለእጅ ተያይዘዉ እስከዛሬ በመላዉ ኢትዮጵያ የሚንቦገቦገዉን የለዉጥ ችቦ በለኮሱበት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ግቢ ዉስጥ ዛሬ ተማሪዉን በዘርና በጎሳ አጥር ታጥሮ ማየት ወያኔ የጣለብን የታሪክ ጠባሳ ነዉ። አገሩንና የአገሩን አንድነት የሚወድ ኢትዮጵያዊ ሁሉ "በቃ" ብሎ ካልተነሳ በቀር ይህ የእነመለስ ዜናዊ የበረሃ ፕሮጀክት እነሱ እንዳቀዱት የኢትዮጵያን ደብዛ በማጥፋት ሊጠናቀቅ የቀረዉ ጥቂት ግዜ ብቻ ነዉ። በዚህ የአገር ማጥፋት ወንጀል የሚጠየቀዉ ደግሞ የመለስ ዜናዊና ጓደኞቹ ብቻ አይደሉም። ይህ ጥፋት ሲፈፀም አጁን አጣጥፎ የሚመለከት እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ተጠያቂ ነዉ።

ኢትዮጵያን በተቆጣጠረባቸዉ ባለፉት 19 አመታት ዉስጥ ወያኔ ሦስት በብሔራዊ ደረጃ የተካሄዱ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ምርጫ አካሂዷል። ወያኔ በሚያዘጋጃቸዉ ምርጫዎች ተቃዋሚ ፓርቲዎች መወዳደር እንጂ ማሸነፍ ስለማይፈቀድላቸዉ በዝረራ የተሸነፈበትን የ97ቱን ምርጫ ጨምሮ በዘመነ ወያኔ የተካሄዱትን ምርጫዎች ሁሉንም ያሸነፈዉ ወያኔ እራሱ ነዉ። ወያኔ ምርጫ የሚባል ነገር ገና ስሙ ሲነሳ እንደ አመለኛ በቅሎ ፀባዩ ይለዋወጣል። የአዉሬነት ባህሪዩ ይብሰበትና አንዳንዴ እንደ እብድም ያደርገዋል። ለምሳሌ አንደኛዉንና ሁለተኛዉን ምርጫ ወያኔ ያሸነፈዉ ከራሱ ጋር ተወዳድሮ ነዉ። ሆኖም ህዝብን ማሸበርና መግደል የወያኔ የተፈጥሮ ባህሪይ ነዉና ያለምንም ተወዳዳሪ ባሸነፈበት በ1992ቱ ምርጫ ድምፄ ይከበርልኝ ብሎ የጠየቀዉን የሀዲያ ህዝብ በጭካኔ ገድሏል።

በ1997ቱ ምርጫ ወቅት ከ200 በላይ ሠላማዊ ዜጎችን በግፍ የገደለዉና የህዝብን ዉሳኔ በጠመንጃ ኃይል የቀማዉ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ዘንድሮም እንደገና "ነፃ ምርጫ" በሚል ሽፋን ለአራተኛ ግዜ እራሱን ለማንገስ ዝግጅቱን አገባድዷል።ከ1997ቱ ምርጫ ትምህርት ቀስመናል የሚሉት የወያኔ መሪዎች ቢመረጡም ባይመረጡም አሸናፊ ለመባል ከፍተኛ ዝግጅት ያደረጉበት ምርጫ ቢኖር የዘንድሮዉ ምርጫ ነዉ። ለምሳሌ ባለፉት አምስት አመታት ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎችን የማያላዉሱ ሦስት ህጎች በፓርላማ እንዲፀድዉ አድርጓል፤ ህዝብን ያስተባብራሉ ብሎ የፈራቸዉን እንደነብርቱካን ሚደክሳ የመሳሰሉ የአንድነት ምልክቶችን እስር ቤት ወርዉሯል። በህዝብ ተወዳጅ የሆኑና ከፍተኛ የአመራር ችሎታ ያላቸዉን መሪዎች ከአገር እንዲሰደዱ አድርጓል። ዛሬ የወያኔን ፀረ ህዝብነት በቅርብ የሚያዉቀዉ የኢትዮጵያ ህዝብ ብቻ ሳይሆን መለስ ዜናዊ ለዘመናት ያታለላቸዉ የአዉሮፓና የአሜሪካ ዘመዶቹም ጭምር ወያኔ 4ኛዉን ምርጫ በቀላሉ እንደሚያሸንፍ ደጋግመዉ ተናግረዋል። ወያኔዎች ግን የራሳቸዉን ጥላ የማያምኑ ድንጉጦች ናቸዉና ስፍር ቁጥር የሌለዉ የህዝብን እጅና እግር የሚያስሩ እርምጃዎቸን ከወሰዱ በኃላም ቢሆን የዚህን ያለቀለት ምርጫ ዉጤት ያመኑት አይመስልም።ባለፉት ሁለት ወራት ዉስጥ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በተለያዩ የአገሪቱ ክልሎች ዉስጥ የፈፀመዉ ድብደባና ግዲያ አገራችን ኢትዮጵያን ለምርጫ ሳይሆን ለጦርነት የምትዘጋጅ አገር አስመስሏታል፤ ስለሆነም ዛሬ የአገር ዉስጥና የዉጭ አገር ጋዜጦችና ደኅረ ገፆችን ያጣበበዉ ዜና በወያኔና በተቃዋሚዎች መካከል የሚካሄደዉ ክርክር ሳይሆን ወያኔ በተቃዋሚዎች ላይ የሚያካሄደዉ የድብደባና ግድያ ዜና ነዉ።

ዲሞክራሲን በመገንባት ላይ ባሉ አንዳንድ ታዳጊ አገሮች ዉስጥ ከምርጫ ጋር በተያያዘ በተለይ የምርጫ ዉጤት ሲገለጽ ዜጎች ይደበደባሉ፤ይታሰራሉ ይገደላሉ። በብዙ ታዳጊ አገሮች ዉስጥ እንደዚህ አይነቱ ማህበራዊ ቀዉስ የሚከሰተዉ ምርጫ ከተካሄደ በኋላ ነዉ፤ ኢትዮጵያ ዉስጥ ግን ግድያና አፈና የሚካሄደዉ በ1997ቱ ምርጫ እንደታየዉ ምርጫዉ ከተካሄደ በኋላ ዘንድሮ ደግሞ ከምርጫዉ በፊት ነዉ። ባለፉት ሁለት ወራት በተለያዩ የአገራችን ክፍሎች የወያኔ ታጣቂዎች የፈፀሙት ግድያና ግድያዉን ለመፈፀም የተጠቀሙት የመሳሪያ አይነት - ወያኔ ተዋግቼ ነዉ ያገኘሁት የሚለዉን ሥልጣን በህዝባዊ አመፅ አንጂ በምርጫ እንደማይለቅ በግልፅ ያሳያል።

በትግራይ ክልልና በተለያዩ የኦሮሚያ አካባቢዎች የፈነዳዉ ቦምብና በእነ አቶ አረጋዊ ገ/ዮሐንስ፤ግርማ ካቤ፤ኢታና ኢዶሳና ቢያንሳ ዳባ ላይ የተፈፀመዉን የግፍ ግድያ ለተመለከተ ወያኔ ኢትዮጵያን ወደ ምርጫ ሳይሆን ወደ ጦርነት እየወሰዳት መሆኑን መገንዘብ አያዳግተዉም።እዚህ ላይ አንድ የሚገርም ነገር አለ፤ እሱም "ጠመንጃ እራሱ ገድሎ እራሱ ይጮሃል" እንደሚባለዉ ካድሬዎቹን እስካፍንጫቸዉ አስታጥቆ ህዝብ መኃል የላከዉ ወያኔ ባዶ እጃቸዉን ከዛሬ ነገ እያሉ በፍርሃት የሚንቀሳቀሱትን ተቃዋሚ ፓርቲዎች "አባላቶቼን" ገደሉብኝ እያለ መወንጀል መጀመሩ ነዉ።ይህ በአዞ እምባ የተነከረ ክስ መለስ ዜናዊ ከምርጫዉ በኋላ በተቃዋሚዎች ላይ ለመዉሰድ ያቀደዉን የበቀል እርምጃ በግልፅ ያሳያል። እንደዚህ አይነቱ የተቀነባበረ የወያኔ ተንኮል ደግሞ መለስ ዜናዊ ያለ ምንም እፍረት ለአለም ህዝብ በግልፅ ያሳወቀዉ ጉዳይ ነዉና በፍፁም ሊገርመን አይገባም።

ወያኔ የዘንድሮዉን ምርጫ የሚያካሄደዉ ኪሱን የሚሞሉለትን የአዉሮፓና የአሜሪካ ወዳጆቹን ላለማስቀየም ነዉ እንጂ ምርጫዉን ቢያሸንፍም ባያሸንፍም ሥልጣን ከእጁ እንደማይወጣ ካረጋገጠ ቆይቷል። ዛሬ ወያኔ ዬኔ ነዉ ብሎ በሚጠራዉ በትግራይ ክልል ጭምር ከፍተኛ የህዝብ ተቃዉሞ እየገጠመዉ ነዉ።ስለሆነም በትግራይና በመላዉ የአገሪቱ ክልሎች ከፍተኛ ችግር ይፈጥርብኛል ብሎ የገመተዉን መድረክ በሚል ቃል የሚታወቀዉን የ8 የፖለቲካ ድርጅቶች ስብስብ ባለ በሌለ ኃይሉ እየተዋጋዉ ነዉ። ከሰሞኑ በግልፅ እንደታየዉና እንደተሰማዉ ወያኔ የተቃዋሚ ፓርቲ እጩ ተወዳዳሪዎችን እያሰረና እየገደለ ነዉ፤ከዚህ በተጨማሪ በህዝብ ዘንድ ተወዳጅ በመሆን ላይ ያሉትን የሆኑትን የመድረክን መሪዎች እስር ቤት ሊያጉራቸዉ እየተዘጋጀ ነዉ።በተለይ የወያኔን የተደበቀ ጉድ አብጠርጥረዉ በማዉጣትና ህዝብን በማሳወቅ ከፍተኛ አገራዊ ሚና የሚጫወቱትን ዶክተር መረራ ጉዲናን ከኢትዮጵያ የፖለቲካ ምህዳር ለማጥፋት ከፍተኛ ዘመቻ ጀምሯል። ከማስተማሪያ መሳሪያዎችና ከምርምር መጽሐፍት ዉጭ ሌላ ምንም ነገር እጃቸዉ ዉስጥ ገብቶ የማያዉቀዉን የአዲስ አበባ የኒቨርሲቲ ምሁርና እዉቅ የፖለቲካ ሰዉ- ቦምብና አዉቶማቲክ መሳሪያዎች ይዘዉ ተገኙ ብሎ የወያኔዉ የወሸት ሹም በረከት ስምኦን የመሰረተዉ የፈጠራ ክስ መለስ ዜናዊ የስልጣን ዘመኑን ለማራዘም የማያደርገዉ ምንም ነገር እንደሌለ ያሳየናል ። ይህ "ሊበሏት ያሰቧትን አሞራ ይሏታል ጅግራ" አይነት የዉሸት ክስ የሚያሳየን ወያኔ ምርጫ በመጣ ቁጥር ህዝብን የመግደልና የማሰር ክፉ በሽታ የተጠናወተዉ የማይድን በሽተኛ መሆኑን ነዉ።

በቅርቡ የግንቦት ሰባት የአዲስ አበባ ዘጋቢ በከተማዋ የተለያዩ ክልሎች ተዘዋዉሮ መጪዉን ምርጫ በተመለከተ ብዙ የከተማዋን ነዋሪዎች አነጋግሮ ነበር። ዘጋቢያችን ያናገራቸዉ ወጣቶች በመጪዉ ምርጫ ለመሳተፍ አለመመዝገባቸዉ ብቻ ሳይሆን "ምርጫዉን ማን የሚያሸንፍ ይመስልሃል" ተብለዉ ለሚጠየቁት ጥያቄ መልሳቸዉ- እንኳን ምርጫዉን ማን እንደሚያሸንፍ ማንና ማን እንደሚወዳደሩም አላዉቅም የሚል ነበር። ዛሬ ኢትዮጵያ ዉስጥ እድሜዉ 25እና ከ 25 በታች የሆነዉ ትዉልድ መሪ ሲባል የሚያዉቀዉ መለስ ዜናዊን ፖለቲካ ሲባል ደሞ የወያኔን ፖለቲካ ብቻ ነዉ የሚያዉቀዉ። ዘረኛዉ መለስ ዜናዊ ኢህአዴግን የሚተካ ንቁ የፖለቲካ ተሳትፎ ያለዉ ወጣት ትዉልድ አፍረተናል እያለ በተለያዩ መድረኮች ላይ ያለእፍረት ተናግሯል። ሆኖም ከአዲስ አበባና ከተለያዩ የአገራችን ክፍሎች በሚደርሱን መረጃዎች መሠረት የኢትዮጵያ ወጣት በንቃት የሚከታተለዉ የወያኔን ፖለቲካ ሳይሆን የእንግሊዝ ፕሪሚየም ሊግ እግር ካስ ዉድድር ነዉ። ምርጫዉን በተመለከተም ቢሆን የኢትዮጵያን ወጣት ልብ ሰቅዞ የያዘዉ የፊታችን እሁድ የሚደረገዉ አገር አቀፍ ምርጫ ሳይሆን በሚቀጥለዉ ወር ደቡብ አፍሪካ ዉስጥ የሚካሄደዉ የአለም የእግር ኳስ ዋንጫ ዉድድር ነዉ። ወያኔ ይተኩኛል ብሎ በከፍተኛ ጥንቃቄ ወርቃማዉ እያለ ከሚጠራዉ አካባቢ እየመረጠ ዉጭ አገር ድረስ እየላከ ከሚያዘጋጃቸዉ ጥቂት ወጣቶች በቀር አብዛኛዉ የኢትዮጵያ ወጣት ፖለቲካን፤ምርጫን ግድያንና እስርን ነጣጥሎ ስለማይመለከት - ስለፖለቲካ በተጠየቀ ቁጥር መልሱ - ተዉኝ አርፌ በሠላም ልኑርበት ሆኗል።

. . . (ወደ ገጽ 4 ይቀጥላል)

## ምርጫ ወይስ ጦርነት?

ከገጽ 3 የዞረ

በወያኔ ምርጫና ፖለቲካ ተስፋ የቆረጠዉ የኢትዮጵያ ወጣት ብቻ አይደለም። የወያኔን ሦስት ተከታታይ ምርጫዎች በተለይ የ1997ቱን ምርጫ የተመለከተ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ከወየኔ ምርጫ የሚጠብቀዉ ምንም ነገር የለም።ሠላማዊ በነበረዉ በ1997ቱ ምርጫ ልጆቹን የተቀማ አባት፤ ባሏ እንደወጣ የቀረባት ሚስትና ወንድሙንና እህቱን ያጣ ኢትዮጵያዊ በዚህ ገና ሳይጀመር በቦምብ ፍንዳታና በጥይት ጫጫታ በታጀበ ምርጫ ዉስጥ ለአገሩ ለኢትዮጵያ የሚጠቅም ምንም ነገር አለ ብሎ አይጠብቅም።

ሌላዉ ሳይጠቅስ እንዲያልፍ የማንፈልገዉ ነገር ቢኖር ባለፈዉ ምርጫ ድምፄ ይከበርልኝ ብሎ ሠላማዊ ሠልፍ የወጣዉ ህዝብ በጥይት ሲረግፍ አፋቸዉን ዘግተዉ የተመለከቱት የአገራችን የሐይማኖት መሪዎች ባለፈዉ ሰሞን ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ለማናገር ጥያቄ ማቅረባቸዉ ነዉ። ጥያቄዉ የሠላም ጥያቄ ነዉና የሚደገፍ ነዉ። ሆኖም ባለፈዉ ምርጫ ህዝብን የገደለዉና ዘንድሮም በተለያዩ ቦታዎች ግድያና አፈና የሚፈፅመዉ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ነዉ እንጂ ተቃዋሚዎች አይደሉም። ስለሆነም የሐይማኖት መሪዎቻችን ከእዉነት የሚበልጥባቸዉ ምንም ነገር የለምና በድፍረት ቆመዉ "ተዉ" ማለት ያለባቸዉ ባለፈዉ ምርጫ የገደለዉንና ዛሬም በመግደል ላይ ያለዉን ወያኔን ነዉ እንጂ ጥቃት የሚደርስበትን ህዝብ አይደለም።ከሁሉም በላይ ደግሞ እነሱን ወደ ህዝብ የሚልካቸዉ "እኔ እዉነት ነኝ" ያለዉ አምላካቸዉ ነዉ እንጂ የዉሸቶች ሁሉ አባት የሆነዉ መለስ ዜናዊ አይደለም።

ከላይ በመግቢያችን ላይ ለመግለፅ እንደሞከርነዉ ከዚህ የፊታችን እሁድ ከሚካሄደዉ ጦርነት አይሉት ምርጫ የኢትዮጵያ ህዝብ የሚጠብቀዉ ነገር አለ ብለን አናምንም። እንደ ቶማስ ካላየን ለማናምን ተጠራጣሪዎችም ቢሆን የወያኔ ድራማ አይተን የጨረስነዉ ነዉና የዚህ ምርጫ መካሄድ የሚያስየን አዲስ ነገር የለም። ስለሆነም ከዛሬ በኋላ ትግላችን ማተኮር ያለበት ወያኔን በምርጫ ለማስወገድ ሳይሆን ኢትዮጵያ ዉስጥ መንግስትን በምርጫ መቀየር የምንችልበትን ሥርአት ለማምጣት መሆን አለበት። የኢትዮጵያ ህዝብ በየአምስት አመቱ ምርጫ ዉጣ እየተባለ እሱ የመረጣቸዉ ወደ እስር ቤት ሲሄዱ በቃችሁኝ ያለቻቸዉ ደግሞ በግድ ሥልጣን ይዘዉ ሲያሰቃዩት 20 አመታት ተቆጥረዋል። ስለዚህ የፊታችን እሁድ ግንቦት 15 ቀን ማንን እንምረጥ እያለን መልስ በሌለዉ ጥያቄ እራሳችንን የምናሰቃይበት ቀን መሆን የለበትም። ይልቁንም ይህ ቀን ዘረኞችንና አምባገነኖችን ከአገራችን ምድር ለአንዴና ለመጨረሻ ግዜ ለማጥፋት በህብረት ቃል የምንገባበት ቀን መሆን አለበት። ወያኔን ከሥልጣን ለማስወገድ መንገዱ ወያኔ የሚያዘጋጀዉ ምርጫ ሳይሆን ህዝባዊ አመፅ ነዉ።

## ግንቦት 7 ለነፃነት፣ ለፍትህና ለዴሞክራሲ ንቅናቄ የግንቦት 7፣ 1997ቱን ምርጫ አምስተኛ አመት መታሰቢያ በሚመለከት መግለጫ አወጣ

ባለፈው ቅዳሜ ታስቦ የዋለውን የግንቦት 7፣ 1997 ምርጫ አምስተኛ አመት በሚመለከት ግንቦት 7 ለነፃነት፣ ለፍትህና ለዴሞክራሲ ንቅናቄ መግለጫ አወጣ።

ንቅናቄው፥ የሃገራችን ህዝብ በዚህ እለት ለመብቱና ለነጻነቱ መከበር ቀናኢ መሆኑን እንዳስመሰከረ በማስታወስ፤ "የዘውግ፣ የሃይማኖትና የቋንቋ ልዩነቶቹ፣ ገዢዎቹ እንደሚመኙት የመከፋፈያና የባርነት እድሜውን ማራዘሚያ ምክንያቶች መሆን እንደማይገባቸው አሳይቷል" ብሏል። በመጨመርም፥ " 'የሚበጅህን እኛ ብቻ እናውቅልሃለን' ለሚሉት ዘረኛ ገዥዎች 'እኔ ለራሴ አውቃለሁ' የሚለውን የማያሻማ መልእክት አስተላልፏል፡፡" ብሏል።

እለቱን በሚመለከት ለዝግጅት ክፍላችን መልክት የላኩት የንቅናቄው ዋና ጸሃፊ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ፥ "ግንቦት 7ን ስናስታውስ የህዘቡን መልእክቶችና ተሸክሞት የተነሳውን ተስፋ ማስታወስ ተገቢ ነው። ይህንን ተሻግረንም በእዚህ እለት ከምርጫው በኋላ የግንቦት 7ን የህዝብ ራእይና ተስፋ ለመድፈቅ የእብሪት በትራቸውን የሰነዘሩትን ዘረኞችና አምባገነኖች በመቃብራቸው ላይ ህዝብ የናፈቀው የዴሞክራሲ ስርአት መገንባቱ የማይቀር መሆኑን ልናሰገነዝባቸው የሚገባበት እለት ነው" ብለዋል።

ግንቦት 7፣ 2002፤ የግንቦት 7 ንቅናቄ ከተመሰረተ ሁለተኛ አመቱን ያስቆጠረበት ቀንም ነው። ይህንን በሚመለከትም አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ፥ "ይህ እለት በሃገራችን ታላቅነቱና ታሪካዊነቱ የገዘፈ በመሆኑ ወዳጆቹም ሆነ ጠላቶቹ እንዳይረሱት የግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ የሚል ድርጅት በስሙ አቋመንለታል። በእዚህ እለት እኛም የግንቦት 7 ንቅናቄ አባላት ግንቦት 7 "በረሳሽ የሚረሳ ይርሳኝ" በሚል የገባነውን ቃልኪዳን የምናድስበት እለት ነው። የግንቦት 7 ህልም እውን እንዲሆን ሁሉም ዜጋ የድርሻውን እንዲያዋጣም ድርጅታዊ ጥሪ የምናቀርብበት እለት ነው።" ብለዋል።

## ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ የመድረክ ፓርቲ አመራር አባል በሆኑት ዶ/ር መረራ ጉዲና ላይ የሃሰት ውንጀላን አስተላለፈ

ቅዳሜ ሚያዝያ 30 ቀን በምእራብ ሸዋ ዞን በኢሉ ገላን ወረዳ ሃሰን ረጋሳ በተባለ የፖሊስ አባል ላይ ከተፈጸመው ግድያ ጀርባ የመድረክ ፓርቲ አመራር አባል የሆኑት ዶ/ር ነጋዶ ጊዳዳ እጅ አለበት ሲል የወያኔ አገዛዝ በሃሰት ወነጀለ።

በረከት ስምኦን ለጋዜጠኞች በሰጠው መግለጫ፣ ሶስት ግለሰቦች መያዛቸውን እና ግድያውን እንደፈጸሙም ለፖሊስ መናዘዛቸውን ተናግሯል። እነዚህ ሶስት ግለሰቦችም፣ መንገሻ የተባለ የመድረክ ፓርቲ አባል ግድያውን እንዲፈጽሙ እንዳዘዛቸው እና ቢታሰሩ ዶ/ር መረራ ጉዲና ስለሚያስፈቷቸው ስጋት እንዳይገባቸው ቃል እንደገባላቸው መናዘዛቸውን ጨምሮ ገልጿል።

በተያያዘ ዜና፥ ግድያውን ፈጽመዋል በሚል ተይዘው የታሰሩት ሶስት ሰዎች ሁናቴ በርካቶችን ሲያነጋግር ቆይቷል። በቴሌቪዥን ላይ ቀርበው ኑዛዜያቸውን ካሰሙት ሶስት ግለሰቦች አንዱ የሆነው ብርሃኑ ሸንተማ፣ በመጀመሪያ ላይ ሲቀርብ የለበሰው ከነቴራ ንጹህ ሲሆን፣ ጥቂት ቆይቶ ያው ከነቴራ ፊት ለፊቱ ላይ ደም ተቀብቶ ታይቷል። ከጥቂት ቀናት በኋላ ወነጀለኛ ተብዬዎቹ ፍርድ ቤት ቀርበው ቅጣት ሲቀበሉ ባሳየው የቴሌቪዥን ዘገባም፣ የዚሁ ግለሰብ ከነቴራ አሁንም ደም እንደተቀባ የሚያሳይ ምስል ተላልፏል።

የቴሌቪዥኑ ጋዜጠኞች ግለሰቡ የተባለውን ወንጀል ከመፈጸሙ በፊት በንጹህ ከነቴራው ኑዛዜ ሲያቀርብ ቀርጸውት ይሁን፤ ወይም ከዛ በኋላ ከነቴራው ላይ የተቀባው ደም የሃሰት ይሆን እስካሁን ያልታወቀ ሲሆን፤ ያም ሆነ ይህ የጉዳዩ ተብዬዎቹ ኑዛዜ እና የቴሌቪዥኑ ተከታታይ ዘገባ የተቀናበረ ድራማ መሆኑን አጋልጧል።

በወያኔ ቁጥጥር ስር የሚገኘው የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ድርጅት ለአገዛዙ የሃሰት ምስክር በመሆን እንደሚያገለግል የሚታወቅ ሲሆን፤ ከዛሬ ሁለት ሳምንታት በፊት የአቶ ቢያንሳ ዲባን አሟሟት በሚመለከት ባቀረበው ዘገባም የራሱን እና የአገዛዙን ውሸት ማጋለጡን ዘግበናል። በወቅቱ አቶ ቢያንሳ ዲባ በተፈጥሯዊ ምክንያት መሞታቸውን ያሳያል በሚል ተቀርጾ የታየው የአስከሬን ምርመራ ውጤት፤ የወረዳው ፖሊስ ግን አቶ ቢያንሳ በድብደባ እንደሞቱ ቃሉን መስጠቱን አጋልጧል።

ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ የመድረክ ፓርቲ አመራር አባላትን በሃሰት መወንጀሉን ከጀመረ የሰነበተ ሲሆን፤ እንደተለመደው ተቀናቃኞቹን ወደ እስር ቤት ለመወርወር በዝግጅት ላይ ሳይሆን እንደማይቀር በርካታ ተመልካቾች ይናገራሉ።

## በኢትዮጵያ የሚኖሩ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ሰራተኞች በአገሪቱ ውስጥ ለመንቀሳቀስ ከአገዛዙ ፈቃድ መጠየቅ እንደሚያስፈልጋቸው በወያኔ ታዘዙ

ባለፈው ሳምንት ለዝግጅት ክፍላችን የደረሰ መረጃ እንደሚያሳየው፥ በኢትዮጵያ የሚገኙ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ሰራተኞች በአገሪቱ ውስጥ ለመጓጓዝ ከአገዛዙ ፍቃድ መጠየቅ እንደሚገባቸው በወያኔ መመሪያ ተሰጥቷቸዋል።

ይህ ትእዛዝ የድርጅቱን እና የሰራተኞቹን በነፃነት የመንቀሳቀስ መብት የሚጻረር እንደመሆኑም፣ ድርጅቱ ትእዛዙ እንዲያብራራለት መጠየቁን ለማወቅ ተችሏል።

በተያያዘ ዜናም፥ በአዲስ አበባ የሚገኙ የምእራብ አገራት ኤምባሲዎች ለዜጎቻቸው የማስጠንቀቂያ መልክቶች እየላኩ መሆናቸው ተዘግቧል። የፈረንሳይ እና የአሜሪካ ኤምባሲዎች ከምርጫው ጋር በተያያዘ ጸብ ሊነሳ እንደሚችል ስጋት እንዳላቸው በመግለጽ፣ በኢትዮጵያ የሚኖሩ እና ወደ ኢትዮጵያ ለመጓዝ እቅድ ያላቸው ዜጎቻቸው ጥንቃቄዎች እንዲያደርጉ መክረዋል።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**
**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው፡፡**
**በ 7140፣ 7175፣ 7185 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ እና በ 6100 KHZ በ 49 ሜትር ባንድ**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ፣ ሐሙስ እና ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 ሰዓት እስከ 3:30፤ እንዲሁም ከምሽቱ 2 ሰዓት እስከ 2:30 የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፤ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቄያችን አድራሻዎች እንድታሳውቁን እንገልጻለን፡፡

**ውድ አንባቢዎቻችን**

**ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዮን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን።** g7radio@ginbot7.org